# ሙያ በልብን አላውቅ ብለው

# የሳይበር አውደልዳዮች ወያኔን

# በመረጃ እያገዙ ለትግላችን አደገኛ ሆነዋል።

*ከአስተዋይ በቀለ*

የትግል እቅዳችን በልበ ቢስ የሳይበር አውደልዳዮችና ነጋሪት ጐሳሚዎች እየባከነ ነው። እነዚህ ሰዎች በረዥም ዘመን መራራ ትግልና መስዋዕትነት የተካበተ የፖለቲካ ተመክሮና አስተዋይነት ያላቸው ኢትዮጵያዊያን ምን ይሉናል አይሉም። ከእኛ በላይ ማን አለና ብለው ነው የሚፏልሉት እንጂ የራሳቸውን የትግልና የፖለቲካ እንጭጭነትና ኩታራነት ጨርሰው አይረዱም።

ለአገርና ለሕዝብ ተቆርቋሪ ነን ቢሉም በቅጡ የተጣሉና በከረረ ጠላትነት አቋም የወያኔ ደመኞች አይደሉም። ያችን ልበቢስ አካላቸውን አምቧትረው እዚህና እዚያ የቆሙ ጥራት የሌላቸው የፖለቲካ አውደልዳዮችና አቀንቃኞች ናቸው።

ከቱኒዚያ ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ወዲህማ አዝማች- ፈታውራሪ እኛ ነን እያሉ በሳይበር ላይ የተግባር እቅድና የትግል ሚስጢር ለወያኔ በገሃድ ያቀብላሉ። እባካችሁ ሙያ በልብ ነው ቢባሉም አሻፈረኝ ብለው እጃቸው ይጭራል፣ አፋቸው ይለፈልፋል። በዚህ ቀውጢ ሰዓት ስንጭር፣ ስንቀባጥር፣ ወገናችን ለአደጋና ለሽንፈት ይጋለጥብናል የሚል ልብ፣ ሥጋት፣ ጥንቃቄና ሕዝባዊ ፍቅር የላቸውም።

የማይጽፉት የማይለፈልፉት የተግባር ዕቅድ የለም። አንዱ ያች የሞኝ ዘፈኑን ክተት እያለ ሲያታክተን፣ ኋደኛው ደግሞ አሁን ትብብር ኋላ ውድድር ይለናል። መንግሥቱ ኃይለማርያምን ካኪ አልብስ ብሎ የመከረ ዛሬ ደግሞ ከወያኔ ጋር ተባበሩ ይለናል።

አንዱ የሳይበር አውደልዳይ እስከመቼ ሲል፣ ሌላው የመጨረሻ ደወል ይላል። ይድረስ ለአንድ ወታደር ሲል ሌላው ደግሞ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ይነሳ ይላል። የኢሳያስ አፈወርቂ ሰላይና አምስተኛ ረድፍ ወኪል በቃ ተነስ እያለ ግርግርን ለሻቢያ ወረራ ያመቻቻል። አበደ ግላሱ ደግሞ ግንቦት 20 እንገናኝ እያለ ሕዝብን በጥይት ሊያስቆላ ይደነፋል። እረ- ስንቱ!

በነዚህ ልበ-ቢስ ሰዎች የሳይበር ትፋትና ድንፋታ ተመጋቢውና ተጠቃሚው ወያኔ በመሆኑ ማንኛውንም ተቃውሞና የትግል እንቅስቃሴ ለማክሸፍ ተመችቶት ራሱን እያጠናከረና እያሰናዳ ነው።

ይኽን በውል ባለመረዳት በሳይበር የሚደረገው መቀላመድ ሕዝባችንን እንዳያስጠቃብንና የሰቆቃውን ዕድሜ እንዲያራዝምብን መጠንቀቅ ያስፈልጋል። ለዚህ መፍትሄው ሁሉን ያቀፈ ድርጅት መፍጠርና ሙያን በልብ ማድረግ ነው።